# ስለመሞት በፍቃደኝነት የተደገፈ

Amharic

**በኮሚቴ የተደገፈ ህጋዊና ማሕበራዊ ጉዳዮች**

ከተለያዩ ፓርቲዎች የተቀናጀ የፓርላሜንት ኮሚቴ ሰኔ/ June 2016 ዓ.ም በጠረጴዛ ተቀምጦ ስለ ህይወት ፍጻሜ ምርጫ በፓርላሜንት ሪፖርት ያለው ጥያቄ ቀርቧል።

ኮሚቴው 49 አስተያየት ድጋፍ ሲያቀርብ፤ 29 የሚሆነው ስለ ህመም ማስታገሻ ለሚቀርብ እንክብካቤ እና 18 ደግሞ ስለዘመናዊ እንክብካቤ እቅድ ማሻሻል ይሆናል።

በሰጡት አስተያየቶች ውስጥ የሚካተት ለተደገፈ ሞት ህጋዊ የአሰራር ዘዴ እና በፈቃደኝነት ስለተደገፈ ሞት መንግሥት እንዲያካሂድ የስልክ ጥሪዎች ይካተታል።

የኮሚቴው ንድፈ ሃሳብ ከ1000 በላይ ለሚሆን ማህበረሰብ እና ለኤክስፐርት በቀረበ ጽሁፎች እንዲያውቁ ተደርጓል። በተጨማሪም ኮሚቴው የዓለም አቀፍን ምርምር ጥናት በማገናዘብ እና በፈቃደኝነት ስለተደገፈ ሞት በህጋዊነት ከሚያካሂዱት አገሮች ልምዶች ያገናዝባል።

**የመንግሥት ፍጻሜ**

በታህሳስ/December ወር፤ መንግሥት እንዳወጀው፤ የህይወት ጊዜያቸው እያበቃና መቋቋም በማይችሉት ከባድ ህመምና በማይድን ሁኔታ ለሚሰቃዩ የቪክቶሪያ ነዋሪዎች በፈቃደኝነት ለተደገፈ ሞት ህጋዊነት እንዲያገኝ ለማድረግ እንደሚያስታውቁ ነው።

የታቀደው ህግ አወጣጥ ከኮሚቴ ያቀረባቸው 49 አስተያየቶች ተመሳሳይ እንደሚሆን ነው።

ከመንግሥት በቀረበው እቅድ ላይ ፓርላመንት የድምጽ ምርጫ ያደርጋል። የድምጽ ምርጫው ከፓርላመንት አባልነት ነጻ እንደሚሆን፤ ይህ ማለት በተለያየ መንገድ የድምጽ ምርጫ ለማቅረብ አባላት ባላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች አይገደዱም።

**በፈቃደኝነት ስለተደገፍ ሞት ምክር**

ኮሚቴው ምን ምክር ሰጠ?

- ጐልማሳዎች በተደገፈ ህጋዊ የአሰራር ዘዴ ለመሞት ውሳኔ ላይ እንዲፈቀድላቸው የኮሚቴው ምክር ሲሆን ይህም በከባድና በማይድን በሽታ የሚሰቃዩ ከሆነና በህይወት መጨረሻ ጊዜ ላይ ላሉት በሆነ ሁኔታ ላይ እንዲሞቱ እርዳታ ማቅረብ።
- ሀኮሞችና የጤና ጥበቃ አገልግሎቶች በሞት ድጋፍ ላይ ስለመሳተፍ መቻል በጣም እንደሚቃወሙት ነው።

በፈቃደኝነት ስለተደገፈ ሞት ማን ነው መጠቀም የሚችለው?

- አንድ ሰው ማድረግ የሚችለው:
  - ለአቅመ አዳም የደረሰና ውሳኔ ለመስጠት አቅም ያለው;
  - ማንኛውም የቪክቶሪያ ነዋሪ እና የአውስትራሊያ ዜግነት ወይም የቋሚ መኖሪያ ፈቃድ ያለው;
  - በመጨረሻ ህይወት ጊዜ (ህይወት መጨረሻ ሳምንታት ወይም ወራት ሲቀር);
  - በከባድ ህመምና በማይድን ሁኔታ ለሚሰቃዩ፤ ይህም ህመሙን መቋቋምና መታገስ ለማይችል በሽተኛ;
  - በራሳቸው ጥያቄ ካቀረቡ;

VICTORIA State Government | Health and Human Services

- ክህመም ጋር ሲታገል ላሳየ የሞት ድጋፍ ጥያቄ እና ሶስት ጊዜያት መጠየቅ - የመጀመሪያው በቃል ጥያቄ; ከዚያ መደበኛ ጽሁፋዊ ጥያቄ ይህም በሁለት ነጻ ምስክሮች የተፈረመበት; ከዚያም የመጨረሻ በቃል ጥያቄ አቅርቦት; እንዲሁም
- በመጀመሪያና ሁለተኛ ሀኪም ተጽእኖ በሌለበት ሁኔታ መገምገም አለበት። ግለሰቡ ስላቀረበው ጥያቄ በሚገባ ስለመነገር፣ እርካታ ስለማግኘቱ እርግጠኛ መሆን ያደረጉትን ምርመራ ማስረዳት የነሱ የሥራ ድርሻ ነው።

<u>በፈቃደኝነት ስለተደገፈ ሞት ማን ነው መጠቀም የማይችለው?</u>

- በፈቃደኝነት ስለተደገፈ ሞት ፈቃድ ለማግኘት ቅድመ ሁኔታው በጣም ጥብቅ እንደሆነና ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በፈቃደኝነት ለተደገፈ ሞት ፈቃድ እንዳያገኙ ይታገዳሉ;
  - በአእምሮ ጤና ብቻ ለሚሰቃዩ ሰዎች
  - እድሚያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ህጻናት
  - በወራት ወይም በሳምንታት የመጨረሻው ህይወት ጊዜ ላልሆኑ ሰዎች
  - በከባድ ህመምና በማይድን በሽታ ሁኔታ ላልሆኑ ሰዎች
  - ህመምን መቋቋም የማይቻል ስቃይ ለሌለባቸው ሰዎች
  - በራሳቸው ለመጠየቅ የማይችሉ ሰዎች።
- በፈቃደኝነት ለተደገፈ ሞት ቀደም ብሎ መጠየቅ ለማይችል ግለሰብ፤ ለምሳሌ፡ ቀደም ብሎ በሚቀርብ የእንክብካቤ እቅድና ቀደም ብሎ ለእንክብካቤ ህጋዊ ትዛዝ።
- በፈቃደኝነት ስለተደገፈ ሞት ሌላን ሰው ወክሎ መጠየቅ አይችልም። ጥያቄው ከሰዎቹ መምጣት እንዳለበትና ይህም ሁልጊዜ በፈቃደኝነት መሆን አለበት።

**ቀጣይ እርምጃዎች**

- ኮሚቴው በህጋዊነት ለተደገፈ ሞት ግልጽ የአሰራር አውታር አቅርቧል፤ ይሁን እንጂ መከሰት ስለሚችል በድህንነትና መከላከል ጠንካራ የሆነ ተግባራዊ የአሰራር መዋቅር ለማካሄድ ከዚህ በበለጠ ሥራ ይፈለጋል።
- መንግሥት ከክሊኒካ፤ ህጋዊና ተጠቃሚ ኤክስፐርቶች የተውጣጡ የኤክስፐርት ሚኒስትራዊ መማክርት ፓናል ውይይት (የውይይት ፓናል) አቋቁሟል።
- በፈቃደኝነት ለተደገፈ ሞት በህጋዊ አሰራር አውታር በተዛመደ ዝርዝር መግለጫ ለማሻሻልና ለማካሄድ በኮሚቴው የቀረበን የጥናት ግኝቶችና አስተያየቶች በኤክስፐርቶች ምክርና ግምት ውስጥ እንዲገባ ማድረጉ የውይይት ፓናል ሥራ ድርሻ ይሆናል።
- ስለሚያካሂደው እድገትና አፈጻጸም፤ ኤክስፐርቶችና ልምድ ያላቸውን በጣም ጥሩ በሆነ መንገድ ከመገልገያ፣ ከድህንነት ተከላካይ እና ድህንነቱ በተጠበቀ የተደገፈ ሞት አሰራር አውታር ስለመፍጠር ተግባራዊ ግምት ከማካሄድ ጋር በተዛመደ ጉዳዮችን እንዲያቀናጁ ከተለያዩ የውይይት ፓናል ቁልፍ ከሆኑ የሥራ ተቋራጮች ጋር በጣምራ ይሰራል።
- እንደ መማክርት ሂደት አንዱ አካል የውይይት ወረቀት እንደሚቀርብና ይህም ተግባራዊና ጠንካራ የደህንነት መከላከያን ያካተተ ርህሩህ ህጋዊ የሆነ የአሰራር አውታር ለመፍጠርና ለውሳኔ መምሪያ ለማውጣት እንዲረዳ ጠቃሚ የሆኑ ጉዳዮችንና ጥያቄዎችን ለይቶ ልማወቅ ነው።
- በሚያዚያ/April 2017 ዓ.ም ለፓነል መወያያ የጊዜያዊ ሪፖርት ይሰጣል እንዲሁም የመጨረሻው ሪፖርት በሐምሌ/July 2017 ዓ.ም ይሰጣል።

- በፓናል ውይይት የሚታዩ መስኮች ላይ የሚካተት:
    - በመጨረሻ በሚቀርበው ሪፖርት ላይ የተጠቀሙ ቃላት እና ግልጽ የህግ ረቂቅ ጽሁፍ በሚወጣበት ጊዜ ጠቃሚ የሆኑ አገላለጽ።
    - በህጋዊ አሰራር አውታር ውስጥ የፈቃድ ቅድመ ሁኔታው በሚገባ እንደተገለጸ ማረጋገጥ።
    - ለግለሰቦችና ለተዋሃደ ማህበረሰብ በፈቃደኝነት ከሚደረግ ሞት ጋር በተዛመደ ማንኛውንም ችግር እንዴት መቀነስ እንደሚቻል።
    - በፈቃደኝነት ለሚደረግ ሞት ጥያቄ ግምገማ ለማካሄድ ስለሚፈጠር ችግር ደህንነቱን ማረጋገጥ።
    - የጤና ባለሙያ ህሊና ችሎታ ነጻነት መጠበቅ።
    - ትክክለኛ የሆነ የስህተት አሰራር ዘዴ መፍጠር።
    - አሁን ካለው የጤና ጥበቃ አሰራር ጋር ተባብሮ መስራት።

Authorised and published by the Victorian Government, 1 Treasury Place, Melbourne.
© State of Victoria, Department of Health and Human Services, February, 2017. (1701015)
Available at https://www2.health.vic.gov.au/about/health-strategies/government-response-to-inquiry-into-end-of-life-choices-final-report